# ምነው ፣ ባቅም ቢሆን

ስለ ሰላም ብለን ፣ ትላንትን ብንረሳ
ምነው ኢትዮጵያችን ፣ በዛባት አበሳ
አሰሱም ገሰሱም ፣ ዛሬ እየተነሳ
ባለ ሜጫው ፣ ጀዋር ፣ እዝቅኤል ጋቢሳ
የቁጩ ዶክተሩም ፣ ፀጋዬ አራርሳ
መንፈራገጥ በዛ ፣ መዝለል ደንገላሳ
በዝንጀሮ ጎፈር ፣ ሆኑብን አንበሳ ።

ሁሉ አዋቂ ሆኖ ፣ ትልቁ ትንሹ
ገብተው ሲያበራዩ ፣ ታሪክ ሲያበላሹ
በየአደባባዩ ፣ ቅርሻት ሲያቀረሹ
ነገርን ለማብረድ ፣ ህዝባችን ታጋሹ
ትዕግስት ቢያሳያቸው ፣ እንዳሻ ሲዋሹ
ወንድ የጠፋ ባገር ፣ ሁሉን ያኮላሹ
መሰላቸው መሰል፣ ከፍልሚያው የሸሹ ።

ባዛውንቶች ተረት ፣ ልክ እንደ ብሂሉ
ሰው ጥራ ተብሎ ፣ እራሱ መጣ አሉ
አጋጣሚ ሲገኝ ፣ ሁሉም ይንጫጫሉ
ታሪክ ልንማር ነው ፣ ዛሬም ከሃጫሉ
ያውም የአድዋውን ፣ እንዲህ በቀላሉ
እነ ሁሉ አማረሽ ፣ ቀላል ያሾፋሉ?
ለባንዳ መጠሪያ ፣ ጎበና እንዳላሉ
ቃላቸውን አጥፈው ፣ ዛሬ ሸብለል አሉ
ትንንሹም ዘውጌ ፣ ሰማይ ተሰቀሉ ።

ባዝማሪነት ሙያ ፣ ስላቀነቀነ
ቢጨበጨብለት፣ መስሎት የጀገነ
ልቡ እስኪፈነዳ ፣ በትዕቢት ታፈነ
ስለ ሁሉ አዋቂ ፣ ሆኖ ተጀነነ
ታሪክ አስተማሪው ፣ ከሮኬት ፈጠነ
ምነው ፣ ባቅም ቢሆን ፣ እየተመዘነ
ፍፃሜ መች ያምራል ፣ እንደተወጠነ ።

ታዛቢው

March 4, 2019